<u>የት አባቴ! ሞትም ይሙት!</u>

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ስሞት የልብ ልብ አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፥ እንዳታስደስቱት።
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ሰበታና፥በዘፈን ሆዬታ አካትቼ
በሠርጌ ብቀበር ሞቼ
እፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሴን ባታፈርሱ።

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ በሳቅ ጉዞ ፍታት ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፊትሽ አይክሰል
በእልልታ ብርሃን ይንበልበል፤
በእረፍቴ እንዳታፌዥብኝ
በሠርጌ እንዳታለቅሽብኝ።
ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ
ልብሽ በኀዘን አይላበስ
በሆድሽ ሞት አይፀነስ
ፅንባ በአይንሽ አይቋጠር
የሞት ቅስሙ እንዲሰበር።
አዎን፥ አደራ፥ አደራችሁ፥ የሙት ውሴን ተቀበሉኝ
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አይደለም፥ ለፍሥሐ እረፍት አብቁኝ፤
በዶርዜ እስክስታ አስቀብሩኝ
በእልልታው ጉዞ አሳጅቡኝ
በጠሩ ችቦ አሳጥሩኝ፤
ጭብጨባችሁን በሰልቱ ይውረድ
ዛፍ ቅጠሉም አብሮ እስኪረግድ፤
ሀገር ምድሩም ያቅራራ
ሀሴት ነው ይበል፥ ጆቢራ
ሠርጌ ነው፥ ይምታ ዳንኪራ።
እንዲህ ስሜት ሲፍለቀለቅ፣ ሲፈነድቅ ሲግል ሃሞት
ቱማታው ሲዋጥ በላቦት
ሆዬታ በሆዬታ ሲራኮት
ማሳለፊያ መግቢያ ሲያጣ፥ ፍርሃት ገበናው ሲራቆት
መቃረቢያ ፍንጭ ሲያጣ፥ በእልልታ ሲወገር ብሶት…
ብቻ ነው፥ ሞት ራሱ እሚሞት።
እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ሞትም አብሮኝ ይሙት!
በእልልታችሁ ግደሉት
በዳንኪራችሁ ውገሩት
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት።

ብላቴን ጌታ ጸጋዬ ገብረ መድኅን
(*፲፱፺፫* - ዶርዜ ሠፈር)